# የዚያን የጀግና ትውልድ ራዕይ ለማሳካት እንደገና እንሰባሰብ፤ እናሰባስብ፤ እንደራጅ፣ ለተሰባሰቡት ተረካቢዎች እናስተላልፍ!!

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በነፃነት ታፍራና ተከብራ ኖራለች። አኩሪ የታሪክና የባሕል ቅርሶች ያላት ሀገር ነች። የነፃነት፣ የገናና ታሪክና የአሸብራቂ ባሕሎች ባለቤት የሆነችው ያለጥርጥር የታላቅ ሕዝብ ሀገር ስለሆነች ነው። ወጣቶች ከወላጆቻቸውና ሰፊ ካለው ከኅብረተሰቡም በርካታ ነገሮች ቀስመው ነው የሚያድጉት። ከወላጆቻቸው በሚተላለፋላቸው በጎ ነገሮች ሁሉ የመንፈስ እርካታን፣ መሠረት የሚሰጥ የታሪክና የባሕል ዕውቀትን፣ የሀገርና የወገን ፍቅርን፣ በራስ የመተማመን ስሜትን፣ ራስን ማወቅን ያገኛሉ። የማንነታቸውንም በርካታውን ክፍል የሚያገኙት በዚሁ መንገድ ነው ማለት ይቻላል። አልፎ አልፎ እንደ ትውልድ ጎላ ያሉና ታሪካዊም የተባሉ እንቅስቃሴዎችን ያደረጉ ወጣቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የበቀሉት ያለምክንያት አይደለም። ይህ ወደፊትም ልንጠብቀው የሚገባ ነው።

ከቅርቡ ታሪካችን ብንነሳ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን በወረሯት ጊዜ አውሮፓውያኑም መንግሥታት አብረው ሲያሴሩብን ጥቁር አንበሳንና ሌሎችንም የአርበኞች ቡድኖች መሥርተው ጠላትን አምስት ዓመት ሙሉ በዱርና በገደል ዕረፍት ነስተው ያንቀራጠጡት ወጣት ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ከእናቶቻችን ጡት ከምንመገምገው ወተት ጋር አብረን የምናገኘው ጠረንና ላብ የወላጆቻችንንና የሀገራችንንም ፍቅር ነው የሚያሳድርብን። ከጣሊያን ወረራ በኋላም በትምህርት ዓይኑን እየከፈተ የመጣው ወጣት ትውልድ የወገኑ ኑሮ እንዲሻሻል፣ ሀገሩም እንድታድግና እንትበለጽግ ይመኝና ይፈልግም ጀመረ። ከነገርማሜና መንግሥቱ ነዋይ የመፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ በኋላ ይበልጥ እየተጋለጠ የመጣው ጨቋኙ የባላባታዊ ሥርዓት ለዚያ ትልቅ ሕዝብ መብቱን፤ እኩልነቱን፣ መሻሻልንና ዕድገትን እንዳላስገኘለት፣ እንዲያውም ለገዥዎች የቅንጦት ኑሮ ሲባል እያቀረቀዘው እንደሆነ ወጣቱ ትውልድ ተገነዘበ። ያ በወገን ፍቅር ታንጾ ያደገው ወጣት ትውልድ ለዘመናት ሲማቅቁ የኖሩት ወገኖቻችን ከጭቆናና ከብዝበዛ ተላቀው እንደ ዜጋ መብታቸው ተከብሮ እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ተነሳሳ። የብሄረሰብ ጭቆናን ዋናው ጥያቄያቸው አድርገው የታገሉትም የወቅቱ ወጣት ኢትዮጵያውያን ባመኑበት መንገድ አሮጌውን ሥርዓት ታግለዋል፤ መስዋዕትም ከፍለዋል። የዚያ ለውጥ ለማምጣት የታገለው ትውልድ አባላት በርካታዎቹ ትግሉ የሚጠይቀውንም መሥዋዕት በውድና በክቡር ሕይወታቸው ጭምር ከፍለዋል። ከአምስት አሥርተ ዓመታት በፊት ጀምሮ ታጋዩ ወጣት ትውልድና ከተጨቋኝና ተበዝባዡ ወገንም ነቃ ያለውና በመጠኑም ቢሆን በሙያው ተደራጅቶ የነበረው ክፍል ያነሷቸው መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች አሁንም በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ገና ምላሽ አላገኙም። ያ ጀግና ትውልድ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን አንስቶ የከፈለው መስዋዕትነት መና እንዳይቀር እንዲሁም በጋራ ያነሳናቸው ጥያቄዎች

እስኪመለሱ ድረስ ትግሉን መቀጠል አሁንም በሕይወት ካሉት የዚያ ትውልድ አባላትና ከዚሁ ጀግና ትውልድ ተረካቢ ከሆኑት ተከታታይ ትውልዶች ብዙ፣ በጣም ብዙ ይጠበቃል። የዚያ ትውልድ አባላት ለለጣቂዎቹ የሚያስተላልፏቸው በርካታ እሴቶች አሏቸውና መልክና ሥርዓት ባለው መንገድ ማስተላለፍ አለባቸው። ለዚህም ባለፉት አያሌ አሥርተ ዓመታት ካካበታቸው ልምዶች በመነሳት የተጀመረውን ሆኖም ግን ያልተጠናቀቀውን ትግል ከግቡ ለማድረስ በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ማደራጀት፣ እየታገሉ ማታገል፣ አብሮ በመታገል ሂደት ውስጥ ከቀደምቱ የቀሰማቸውንና ከራሱም ተመክሮ ያገኛቸውን ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። ይህ ሊደረግ የሚገባው እየሠሩ በማሳየት፣ እየተደራጁ በማደራጀት፣ እየታገሉም በማታገል ህያው በሆነ መልክ ነው። ያኔ በርግጥ የተግባር ትስስር፣ የገድል ድልድይ ፈጥረን፣ እንደ እናት እትብት የወገናችንን ፍቅርና የኢትዮጵያዊነት መተላለፊያ ሆነን ትውልዶችን በተፈተነውና በመጠቀ ራዕይ ላይ በተመሠረተ ገድል እናቆራኛለን። ስለሆነም በአዲስ የትግል መንፈስ በተጠናከረ መልክ ተደራጅቶ ለመታገል እንዲቻል ውይይት ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ይህ አጭር ጽሁፍ ቀርቧል። ጽሁፉ ሰባት ዋና ዋና ክፍሎች ያቀፈ ነው። እነሱም፦

I. የዚያ ትውልድ ዓላማዎች የመጠቁ ራዕዮችን ገላጭ ናቸው።
II. የዚያን ትውልድ ራዕይ የሶሻል ዴሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለም በበቂ ይገልጠዋል።
III. የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማሳካት የሚጠብቀን ሥራ ግዙፍ ነው።
IV. ይህንን ከባድ ሥራ የአንድ ወይም የጥቂት ድርጅቶች አባላት ብቻቸውን ሊወጡት አይችሉም።
V. የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማሳካትና ጎያው አድርጎም ለማቆየት በስፋት መልሶ መሰባሰብን፣ ጠንካራ ድርጅት መፍጠርን ይጠይቃል።
VI. መልሶ መደራጀት እንዴት? መንገዶቹ ምንድን ናቸው? በተለይ ወጣቱን ትውልድ እንዴት አድርጎ ለማሰባሰብ ይቻላል።
VII. በዚህ መሠረታዊ ሠነድ ውስጥ የሰፈሩትን መሪ ሃሳቦች ከሚቀበሉ ግለሰቦችና የተደራጁ ኃይሎች አባላት ምን ይጠበቃል?

## I. የዚያ ትውልድ ዓላማዎች የመጠቁ ራዕዮችን ገላጭ ናቸው

ትውልዱ ከፍተኛ የሀገርና የወገን ፍቅር ያለውና ትልልቅ ዓላማዎችን አንግቦ የተነሳ፤ የታገለና ያታገለ ስለሆነ እነዚህን ዓላማዎቹን፤ የኛና የሕዝባችንም ስለሆኑ ዛሬም እንደወትሮው በግልጽነትና በጽናት እንቁምላቸው፤ መልሰን እናለምልማቸው፣ እናሳድጋቸው፣

እንታገልላቸው። የዚያ ትውልድ ፍላጎቶች በሚከተሉት አውራ ሃሳቦች ሊጠቃለሉ የሚችሉ ናቸው ብለን እናምናለን፦

ሀ) ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ባለሙሉ መብት መሆን እንዲሁም ለሀገራዊ ሉዓላዊነት መቆምና መታገል።

ለ) ሕዝብ ያለሀገር ባለ ሙሉ መብት ሆኖ መኖር ስለማይችል፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ኅላዌ እንዲጠበቅና ሀገራዊ አንድነቷ እንዲረጋገጥ መታገል።

ሐ) ለሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የዜግነት እኩልነትን ለማረጋገጥ መቆምና ጸንቶም መታገል፤ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ በዘሩ (በብሄር/ብሄረሰብ)፤ በሃይማኖቱ (በዕምነቱ)፤ በፆታው፤ በዕድሜው፤ የሃብትና የንብረት ባለቤት በመሆኑ/ባለመሆኑ ላይ የተመሠረተ ልዩነትና አድሎአዊነት በሕግ ፊት እንዳይፈጸምበት ያለማወላወል መታገል። የሕዝባችን አንድነት በእኩልነቱ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ።

መ) ያ ትውልድ ለብሔር/ብሔረሰብ መብት መረጋገጥ ሲታገል በእኩልነታቸው ላይ የተመሠረተ አንድነታቸውንና የሀገሪቱንም አንድነት ለማስጠበቅም ጭምር እንጂ በጠባብ ብሔረተኛነት አስተሳሰብ ተቃኝተውና ተመርተው እርስ በርስ እንዲጋጩና ሀገራችን እንድትበታተን ለማድረግ አልነበረም። የትውልዱ ዕምነት ማንም መጨቆን የለበትም የሚል ነው። ሃቁን በትክክል ባልተረዱት ወይንም በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ ከዚህ ጥያቄ ጋር ተያይዞ በትውልዱ ላይ የሚሰነዘረው ወቀሳ መሠረተቢስ መሆኑን በአጽንዖት ማስረዳት ይገባናል። ተዛብቶ የነበረውን ኢ-ፍትሃዊ የነበረውን ግንኙነት በመለወጥ የሕዝባችን እኩልነት ለማስገኘት በማሰብ እንጂ አንድነቱን ለማናጋት በመፈለግ አልነበረም ያ ትውልድ የብሔር/ብሔረሰብ መብት ጥያቄን በወቅቱ ይቀርብ በነበረበት መልክ ያነሳው፣ ኤርትራን ለማስገንጠል ወይንም የተገንጣዮች መሣሪያ ለመሆን አስቦ አልነበረም፣ የወደፊቱን ጉዞአችንም በዚሁ መሠረት እንዲስተካከል ያሻዋል፣ እርማት ያስፈልጋልና።

ሠ) ያ ትውልድ ስለወገኑና ስለሀገሩ የነበረውን በጎ ፍላጎትና ራዕይ በበቂ የሚገልጽለት አስተሳሰብ ሲፈልግ ነው በወቅቱ በዓለም ውስጥ በጣም ጎልቶ ይታይ የነበረውን ባመዛኙም የሚመኘውን ሁሉ ያቅፍ የነበረ የማርክሲስት-ሌኒኒስት አስተሳሰብ ከፊቱ ተደቅኖ ያገኘው። ቅኝ ገዢነትና ዘረኝነትን ያራምድና በይፋም ይደግፍ ከነበረው የከበርቴው ርዕዮት ደግሞ በርግጥም የተሻለ ነበርና ያንን ርዕዮት በመቀበሉ ያ ትውልድ ሊወገዝ አይገባውም።

ረ) ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በተለይም በወቅቱ የነበረው የጉልተኞች ንጉሣዊ ሥርዓት ውስጥ ይታይ የነበረውን ማንኛውንም ኢ-ፍትሀዊነት ያ ትውልድ አምርሮ ተቃውሟል። ለሕግ የበላይነት፤ ለፍትኅ ርትዕ፤ በነፃነት ለሚሠሩ የዳኝነት ተቋሞች መተከልና ዕምነትም መስፈን፤ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የቆመ ትውልድ

ነው። ያ ትውልድ ለተበደሉት ሁሉ፣ ለሚጨቆኑት ሁሉ ጥብቅና ቆሟል፣ ተገቢም አስፈላጊም ስለነበረ ያንን አድርጓል። ዜጎች የሕይወት ዋስትና እንዲያገኙ የሚፈልግና ይህንም ዓላማውን ለማሳካት ጠንክሮ የታገለ ትውልድ ነው።

ሰ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወትና አኗኗር እንዲሻሻልና እንዲለወጥ የቆመና የሚፋለም ትውልድ ነው፤ ትምህርት እንዲስፋፋና ድንቁርና እንዲጠፋ፤ የጤና ጥበቃና የህክምና አገልግሎቶች እንዲስፋፉና ዜጎች ጤናማ እንዲሆኑ፤ የኤኮኖሚ ግንባታ ተስፋፍቶ ሥራ አጥነት እንዳይኖር፤ ምርትና ምርታማነት አድገው እጦትና ድህነት/ረሃብና እርዛት እንዲጠፉ፤ የሕዝብ እኩልነት መብት እንዲረጋገጥ፣ ... ወ.ዘ.ተርፈ የታገለና ያታገለ፣ የሚታገልም ትውልድ ነው።

የዚያ ትውልድ ራዕይ ቢያንስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ያካተተ እንደነበር አያጠያትቅም።

1. ከረሃብ፤ ከችጋርና ከሰቀቀን ሕዝባችንን ለማላቀቅ፤
2. ሕዝብ የጤና ጥበቃና የህክምና አገልግሎት በነጻ የሚያገኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር፤
3. ዕድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ዜጎች ሁሉ ሁለተኛ ደረጃን እስከሚያጠናቅቁ ድረስ በነጻ ትምህርትን ለማግኘት እንዲችሉ፤
4. ሥራ አጥነትን ለማስወገድ ይቻል ዘንድ ያልተቋረጠ ጥረት በማድረግ ሁሉም ሠርቶ ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር፤
5. እያንዳንዱ ዜጋ የመኖር ዋስትና እንዲያገኝ፤ ጸጥታው ተጠብቆለት በሠላም ለመኖር እንዲችል ማድረግ፤
6. የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ለማድረግ፤
7. የሕግ የበላይነት፤ የዳኝነት ተቋም ነፃነት እንዲረጋገጥ፤
8. የዜጎች እኩልነት መብት እንዲረጋገጥ፣ (በብሄር/ብሄረረሰብ፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ምንም ዓይነት ማበላለጥ እንዳይኖር)፤
9. ማንኛውም ዜጋ ሥራ በሚያጣበት ወቅት የመኖር ዋስትና እንዲያገኝ፣ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ለልመና እንዳይዳረግ፣ ሲያረጅ ወይንም የአካል ጉዳት ሲደርስበት መጠሪያ እንዲያገኝ፣
10. ሴቶች በእርግዝናቸው የመጨረሻ ወራትና ከወለዱም በኋላ የሚያገኙት ክፍያ ሳይጓደል የወሊድ ፈቃድ ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲኖር፤
11. ሕፃናት ልዩ እንክብካቤ እንዲያገኙ፣ ቢያንስ በከተሞች ውስጥ ነፃ የመዋዕለ ሕፃናት ግልጋሎቶች እንዲኖሩ፤
12. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመሬትና የሌላም ንብረት ባለቤት የመሆን መብቱን ማረጋገጥ፤

13. ማንኛውም ዜጋ ሠርቶ ተገቢውን የጉልበቱን ዋጋ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ እንዲኖር፣ በሙያና በሠራተኛ ማኅበር ሊደራጅና ሊደራደርም የሚችልበት ሁኔታ እንዲያገኝ፤
14. አርሶአደሮችም መብታቸውን ለማስከበር በሚያስችሏቸው ማኅበሮች ሊደራጁና ሕይወታቸውን ለማሻሻልና ለመለወጥ እንዲችሉ፤
15. እያንዳንዱ ዜጋ መከበርና ማደግም የሚችለው ሀገሩ ስትኖርና የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ለሕዝቡ ጥቅም የሚውልበት ሁኔታ ሲፈጠር ነውና፣ የሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት እንዲጠበቅ ማድረግ የሁሉም ዜጋ መብትና ግዴታም መሆኑ ግንዛቤ ሊያገኝ እንዲችል፤
16. ለሀገር ልማት ሰላም እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በሀገር ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን፤ ከጎረቤት ሀገሮች ጋርም በሰላምና በመከባበር ላይ መኖር እንዲቻል ማድረግ...ወ.ዘ.ተርፈ ናቸው ማለት ይቻላል።

## II. የዚያን ትውልድ ራዕይ የሶሻል ዴሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለም በበቂ ይገልጠዋል

ዋና ዋና የማኅበራዊ ፍትኅ ጥያቄዎች አጥጋቢ በሆነ ደረጃ ለመመለስ የሚያስችሉ ዓላማዎችን ያካተተ የፖለቲካ ራዕይ፣ እንደዚህ ያለ ራዕይን ያነገበ የፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ ሁሌም በሀገራችን እንዲኖር፣ በፍጹም እንዳይዳከም በማድረግ፣ ሕዝቡን ማዕከል ያደረገና በሰፋትም ያሳተፈ ትግል በማድረግ ፍትኅዊ፤ ማኅበራዊና የኤኮኖሚ ጥያቄዎችን በመመለስ ዓላማዎችንም ለማሳካት የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት ሊመሠረት ይገባል። አሁንም እንደወትሮው ለማኅበራዊ ፍትኅ ያለማወላወል ልንቆም ይገባል እንላለን። አብዛኛው ሕዝባችን በድህነት አረንቋ ውስጥ የሚኖር የዕለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን ማሟላት ያቃተው ስለሆነ የዜግነት መብቱ ትርጉም የሚኖረው መሠረታዊ ፍላጎቶች ተጠብቀውለት ለመኖርና ለመሻሻልም ሲችል ስለሆነ ዛሬ እየገፋው ያለው የመከራ ኑሮው ሊሻሻልለት ይገባል። ኤኮኖሚያዊ ጭቆናንና መረን የለቀቀ ምዝበራን በሕግ በማቀብ፤ ሠርቶ በሌው ሕዝብ ከጉልበቱ ዋጋ አግባብ ያለው ድርሻ አግኝቶ የተሻለ ኑሮ ሊመራ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ያ ትውልድ ያደረገው ብርቱ ትግል ዛሬም፤ ነገም መቋረጥ የለበትም።

በሀገራችን ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ አርሶ በሌ ስለሆነ የሚያርሰው መሬት የአራሹ የራሱ መሆኑ አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ብቻ በቂ አይደለም። ምርቱን ለማሳደግ የሚያስችሉት ግብዓቶች ያስፈልጉታል። በአነስተኛ ክፍያ አለዚያም በነጻ የእርሻ ልማት ግብዓቶችንና ምክርም ሊያገኝ ይገባል። ምርት ያለውሃ ስለማይገኝ ድርቅ በሚያዘወትራት ኢትዮጵያችን ውስጥ የመስኖ ውሃ ጉዳይ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። ገበሬዎች በቂ ምርት አግኝተው

ሀገራችን በምግብ ራሷን እንድትችል፤ ሕዝቡም ከርሃብ እንዲላቀቅ አራሹ ሕዝብ መሬት፤ ውሃ፤ በሀገር ውስጥ የሚሠራ ማዳበሪያ፤ ትራክተሮችና ሌሎችም የእርሻ መሣሪያዎች ቢያንስ በማኅበር ደረጃ፤ የእርሻ ዕውቀት ካላቸው ባለሙያዎች አስፈላጊውን ምክር ቀጣይነት ባለው መንገድ ሊያገኝ ይገባል። የገጠሩን በርካታ ሕዝባችን ኑሮ ማሻሻል መቻል በርካታ ተዛማጅ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

ዕድሜአቸው በትምህርት መቀሰሚያ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሆኑ ልጆች በሙሉ ለመማር መቻል አለባቸው። የትምህርት ፖሊሲ ወጣቱን ትውልድ ራሱን ከመቻልም በላይ ለሀገር ልማትና ዕድገት የሚያዘጋጅ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕድገትንም የሚያስገኝ ሊሆን ይገባል። ወጣቱ ትውልድ ጥሩ ትምህርት እንዲያገኝ ለማድረግ የሚቻለው ብቃት ያላቸው መምህራንን ሲያገኝና ለትምህርት የሚያስፈልጉት መጻሕፍትና ቁሳቁሶች በበቂ ሲያገኝና ሌሎችም መሰናክሎች ሲወገዱለት ነው። ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ምግብ፤ ልብስ፤ መጠለያ፤ ሕክምናና ለትምህርት የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶችን በሙሉ በነጻ ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ይገባል። ይህ ካልሆነ ትምህርት፣ እንዲያም ሲል ከፍተኛው የሙያና የዕውቀት ዘርፍ ተጠቃሎ የሃብታሞችና የልጆቻቸው ይሆናል። አንድ ጊዜ በማንኛውም መንገድና ዘዴ ሃብት ለማካበት ከቻሉ ወላጆች ለመፈጠር ያልታደለ ሁሉ የትምህርትና ዕውቀት በተለይም የከፍተኛ ትምህርትና ዕውቀት ከነሱም ጋር በተያያዘ ሊገኙ ከሚችሉ ጥቅሞችና ዕድገቶች ሁሉ እየተገለሉ ይቀጥላሉ ማለት ነው። የዚህ ዓይነቱ በርካታዎችን የማያካትት የትምህርት ሥርዓት ኢ-ፍትሃዊ ሁኔታዎችን ያለጥርጥር ስለሚፈጥር ለወደፊቷ ኢትዮጵያ አይበጅምና የትምህርት ዕድልን በተጨባጭ ለሁሉም በእኩልነት ሊያዳርስ የሚችል ፍትሃዊ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት ሊመጣ ይገባል።

በዓለማችን ውስጥ ከሚገኙት በጣም ደሃ ከሚባሉት ሀገሮች አንዷ በሆነችው ኢትዮጵያችን ውስጥ፣ ከተማዎች በሥራ-አጦችና በድሃዎች በተጥለቀለቁባት፣ አብዛኛው ሕዝብ በገጠሮች የሚኖር በሆነባት፣ ከነዚህም ውስጥ አብዛኛው ደሃ በሆነባት ሀገራችን ውስጥ የማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ፍትኅ ጥያቄን መመለስ ለሕዝብ ጥቅም ከተፋለመው ድርጅታችን ሁሌም የሚጠበቅ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያው መብቱን ተጎናጽፎ፣ ሰብዓዊ መብቶቹም ተከብረውለት በመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ እንዲኖር ስለምንፈልግ፣ በተጨማሪም ሥርዓቱ ውስጥ የማኅበራዊ ፍትኅ ጥያቄዎች መመለስ ቁልፍ ሥፍራ እንዲኖራቸው ስለምንፈልግ፣ እነዚህን ዓላማዎቻችንን የሚያካትትልን ራዕይ ማግኘትና መመሪያችንም ማድረግ የፖለቲካ አካሄዳችንን ፈር በማስያዝ አንድ ታዋቂ ረድፍ ላይ ያስቀምጥልናል።

ርዕዮተ-ዓለማዊ መመሪያቸው ተመሳሳይ ከሆኑ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋርም ተቀራርቦ፤ ተጋግዞና አብሮም ሊሠራ የሚቻልበትን ሁኔታ ይፈጥራል። ለሕዝባችንና ለሀገራችን ያለንን ብሩኅ ራዕይ፣ ያሉንን ዝርዝር ዓላማዎቻችን በማካተት፣ በደንብ ስለሚገልጥልን ነው ሶሻል ዴሞክራሲን የመረጥነው። ስለዚህም ትግላችን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሊካተት የሚችል ማኅበርዊ ፍትኅን ለማምጣት ያለመታከት መሥራትና ይህንን በበርካታ ሀገሮች ውስጥ የተፈተነ ርዕዮት ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ በእያንዳንዱ ዘርፍ ያሉትን ችግሮችና መሠናክሎች እንዴት መወጣት እንደሚቻል አጥጋቢ የሆኑ ዝርዝር ጥናቶችን በማድረግ አባላትን፣ ደጋፊዎችን፣ ሰፊውን ሕዝብም ያለመታከት ማሳወቅና ማስተማር ያስፈልጋል።

## III. የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማሳካት የሚጠብቀን ሥራ ግዙፍ ነው

1. አሁን ያለውን የህወሃት/ኢህአዴግ ሥርዓት ለመታገልና ለማቸነፍም መቻል፣ በሁሉም ዘርፎች ውጤታማ ትግል ለማድረግ መቻል፤
2. ተኪውን መንግሥትና ሥርዓት፣ ከሽግግር መንግሥት ማቋቋም ጀምሮ ለማዋቀር የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ፤
3. ሕዝቡን በበቂ ስለ ራዕያችንና እሱንም ይገልጣል ብለን ስለተቀበልነው ርዕዮተ ዓለም ማሳወቅ፤ ማስተማርና ማዘጋጀት፤
4. ሠፊውን ሕዝብ በሀገር ውስጥ ማደራጀትና ማታገልም ያስፈልጋል።

## IV. ይህንን ከባድ ሥራ የአንድ ወይም የጥቂት ድርጅቶች አባላት ብቻቸውን ሊወጡት አይችሉም።

1. የፖለቲካ ድርጅቶች አሁን ከሚያደርጉት እንቅስቃሴዎቻቸው ለመገመት እንደሚቻለው፤ ባሏቸው አባላትና መዋቅሮች ብቻቸውን ከፍ ብሎ የተገለጹትን ተግበሮች ለማከናወን አይችሉም።
2. የዚህ ዓይነቱ በግልጽና ዘላቂ ራዕይ ላይ የተመሠረተ ስትራተጂያዊ ተግባር ደግሞ በኅብረት ግንባር ደረጃ ብቻ ከሚሰባሰቡ ኃይሎች መካከል ሁሉም ላያምኑበት ይችላሉና፣ ወይንም የተወሰኑት ሊቃወሙትም የሚችሉ ስለሚኖሩም በኅብረት ግንባር እንቅስቃሴ ሊታገዝ ቢችልም ከኅብረት ግንባር የላቀ መሰባሰብንና መደራጀትን የግድ ይላል።

V. **የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማሳካትና ጎደው አድርጎም ለማቆየት በስፋት መልሶ መሰባሰብን፣ ጠንካራ ድርጅት መፍጠርን ይጠይቃል።**

1. በዚህ መንደርደሪያ መጀመሪያ ላይ የተገጹትን የዚያን ትውልድ ራዕይ ይዞ የተነሳው ክፍል ሰፊ ነበር፣ ሁሉም የትውልዱ አባል ተመጣጣኝ ግልጽነት ባይኖረውም በርከት ያለው ራዕዩን ተቀብሎ አስተጋብቶታል፣ ባለቤትነትም አግኝቶበታል፣ ከፍተኛ መሥዋዕትም ከፍሎበታል። የዚያ ትውልድ አባላት ያኔ በደረሱት ጉዳቶች፣ ከዚያም በኋላ በተከሰቱ የጤና መታወኮች ሕይወታቸውን ያጡት በርካታዎች ናቸው። ስለዚህም የዚያ ትውልድ አባላት በተለይም ገንቢና ውጤታማ ሥራ ሊሠሩ የሚችሉት ቁጥር እየተመናመነ በመምጣት ላይ ነው፣ ነገር ግን አሁንም በሕይወት ያለው የሰው ኃይል የሚናቅ ቁጥር አይደለም። ስለዚህም በከፍተኛ ጥድፊያ የቆመለትን ሕዝብ ሕይወት ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመለወጥ በሚያስችለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ፣ ይህም ማለት የዚያን ትውልድ ራዕይ ሊያሳካ የሚችል እንቅስቃሴን በመፍጠርና በማንቀሳቀስ ሥራ ላይ ሊሠማራ ይገባዋል እንላለን።

2. ከዚያ ትውልድ የተማረው ክፍል በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ይንቀሳቀሱ በነበሩት የተማሪ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜም ተሳትፏል፣ ከተማሪ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተፈጠሩት በኋላም እንቅስቃሴው በፖለቲካ ልዩነቶች የተነሳ እንዲከፋፈል ምክንያት ከሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ሁለቱ ያኔ ጎልተው የወጡት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እና የመላ ኢትዮጵያ ሶሻያሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ቢሆኑም ሌሎችም ወዝሊግ፤ ኢጭአት፤ ማሌሬድ የሚባሉ ነበሩ። ጭፍጨፋው ከመጀመሩ በፊት በቅንነት አብዮታዊ ሠደድ የተባለውን በደርግ የተቋቋመ ድርጅት የተቀላቀሉ ሊኖሩ ይችላሉ። ከሁለቱ ድርጅቶች ውጭም የተወሰኑ ተራማጅ የሆኑ ዜጎች እንደነበሩ የማይካደው ሃቅ ነው። በተለይ በሁለቱም ድርጅቶች ውስጥ የተሰለፉት የዚያ ትውልድ አባላት የዚያን ትውልድ ራዕይ አንግበው የተነሱና የታገሉም ናቸው፣ በኋላ ለሠሯቸው ስህተቶችና ጥፋቶች የሕዝቡን ፍርድና ብያኔ ለመቀበል ተዘጋጅተው፣ ከቂምና የበቀል ስሜቶች ተላቀው፣ የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማሳካት ይህን በማድረግም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመካስ በአንድ ጠንካራ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሰባስበው ሊታገሉ ይገባል። በሌሎቹ በኢማሌድኅ ተሰባስበው ከነበሩት ድርጅቶች ውስጥ አባል ከነበሩት መካከልም ከዕውቅ ጨፍጫፊዎችና ፀረ-ሕዝቦች ውጭ ከሆኑት በሚፈጠረው እንቅስቃሴ ውስጥ አዎንታዊ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ይኖራሉ። ሁሉንም ማግለል አይገባም።

3. ከዚያ ትውልድ አባላት መካከል የዚያን ትውልድ ራዕይ ሰፊ አድማስ በተለየ መልክ በመውሰድ የብሄር/ብሄረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የገቡም ነበሩ። ከዜጎች፣ ከመደቦች፣ ወይም ከኀብረተሰብ ጥያቄዎች፣ ከዚያም አልፎ ከዓለም ዓቀፋዊነት ከመነጨ ወገናዊነት በበለጠ ደረጃ በቅድሚያም የብሄር/ብሄረሰብ ጥያቄን እንደመሪ ሃሳብና እንደትግል መመሪያቸው በማድረግ በብሄር መልክ ተደራጁ። በዚሁ ባመኑበት መልክም ለፈለጉት ለውጥ ታገሉ። የተወሰኑት ደግሞ በብሄረሰብ ድርጅቶች ውስጥ የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማራመድ ሞክረው ዛሬ የራዕዩን ፈር መሳት በመረዳት የግልና የቡድን ውሳኔዎች በማድረግ ራሳቸውን ከገቡባቸው ሁኔታዎች አውጥተው በሰፊው የዚያ ትውልድ ራዕይ አድማስ ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ የዚያ ትውልድ አባላት አሁንም የዚያን ትውልድ ራዕይ ለማሳካት በሚደረገው አስፈላጊ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥሩ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

4. በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ፣ እንቅስቃሴው ውስጥ ክፍፍል ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ግን ለአንዱ ወይንም ለሌላው የፖለቲካ ድርጅት በተለያዩ ወቅቶች ድጋፋቸውን ቢሰጡም በፖለቲካ ድርጅት ሳይሰባሰቡ የቆዩ የዚያን ትውልድ ራዕይ ግን አሁንም የሚደግፉ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭም የሚኖሩ የትውልዱ አባላት የማይናቅ ቁጥር ያላቸው ዛሬም አሉ። ከእነዚህ መካከልም ሆነ ከሌሎቹ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት ክፍሎች ውስጥ በአጋጣሚቸው ሁኔታዎች ተሸንፈው ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገው የተውና "በተሸናፊነት" ወይም በኑሮ አስገዳጅነት ለተለያዩ ጨቋኝ ገዢዎች፣ መንግሥቶችና ሥርዓቶች ያገበደዱም መሣሪያ እስከመሆን የደረሱም ይኖራሉ። ያልተሸነፉትን፣ አሁንም የዚያን ትውልድ ርዕዮት እንዳነገቡ ያሉትን ፈልጎ ማግኘትና ማሰባሰብ ይገባል።

5. በተለያዩ ጨቋኝ ሥርዓቶች ውስጥ አገልግለው፣ አሁን ግን በማያወልዳ መልክ በሠሯቸው ስህተቶች በመጸጸትና ራሳቸውንም ከነዚያ ሥርዓቶች ዕምነትና አስተሳሰብ በማላቀቅ በዚያ ትውልድ ራዕይ አድማስ ክልል ለመታገል የሚያስችላቸው ሁኔታዎች ውስጥ እየገቡ ያሉም አይብዙ እንጂ ይኖራሉ። እነዚህንም ከቂምና የበቀል ስሜት ወጥተን በአዲስ መልክ የሚደረገው መሰባሰብ ውስጥ ሚና ሊጫወቱ እንዲችሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኀይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የኢሕአፓና የመኢሶን አባላት አብረው መሥራት መቻል የከፈተውን የይቅር መባባልና ቁርሾን ትቶ የመራመድ ፈለግ ተከትለን አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ የመቻቻልና የመግባባት እንዲሁም የመከባበር መንገዶችን ልንከተል ይገባናል።

## VI. መልሶ መደራጀት እንዴት? መንገዶቹ ምንድን ናቸው? በተለይ ወጣቱን ትውልድ እንዴት አድርጎ ለማሰባሰብ ይቻላል

1. የመንደርደሪያው ሰነድ በደንብ በጥናት ላይ በተመሠረቱ አውራ ሃሳቦችና አቀራረቦች እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ በደንብ ጥራቱ፣ አሳማኝነቱ፣ ስህበቱ በአዘጋጆች ተረቅቆ በአደራጆችም ጭምር እንዲመረመርና እንዲተችበት ማድረግ፤

2. አደራጆችን፣ በመጀመሪያ የተወሰኑ መስፈርቶችን በማውጣት በጥንቃቄ መምረጥ፣ የሚያነጋግሯቸውን ሰዎች በመመደብ በጥንቃቄ መዘጋጀት፣ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በሴሚናር መልክ ተገናኝቶ በሰፊው መምከር። ስለሥራቸው፤ ስለሚከተሏቸው መንገዶች፣ ሥራው ስለሚጠይቀው ጊዜ ግምት፣... ወ.ዘ.ተርፈ፤

3. የተወሰነ የተግባራዊ እንቅስቃሴ አዘጋጅ አካል መሥርቶ፤ መልዕክቶችን ማስተላለፊያ መንገዶችን በተመለከተ በድምፅና በሥዕል ጭምር ማራኪ በሆኑ ቅንብሮች በቪዲዮና በጽሑፍ፣ በመጽሔት መልክ፣ ሃሳቦቹ እንዲቀርቡ፣ እንዲሠራጩም ማድረግ፣ በተለይም ወጣቶችን ሊስቡ በሚችሉ መንገዶች፤

4. የአደራጆችን የሥራ ዕድገት በተመለከተ ተግባሮቻቸውን ዘርዝሮ ከሥራ ጊዜ ሠሌዳ ጋር ሊከናወኑ የሚችሉበትን ጊዜ፣ መልሶ መመርመር ቢቻልም፣ የመወሰን ሃላፊነት ግን ለራሳቸው ለአደራጆቹ መተው፤

5. ለሚመረጡት አደራጆች ሙሉ ሃላፊነቱን በመስጠት እገዛና ትብብር ማድረግ፣ ዕድገቱን ከማወቅ አኳያ ቅርብ ክትትል ለማድረግ መጣር ነገር ግን በአደራጆቹ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ምንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት እንዳይደረግባቸው በቅድሚያ ስምምነት ላይ መድረስ ያሻል፤

6. በቂ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ፣ ከፍተኛ ድምቀትና ተስተጋቦ ሊያገኝ በሚችልበት መድረክ እንቅስቃሴው እንዲታወጅ ማድረግና ለጉባኤም ጥሪ ማድረግ፣ እስከዚያ

ጊዜ በሚሠሩት ሥራዎች ላይ ተመሥርቶ የጉባኤው አዘጋጅ ኮሚቴ በአደራጀች ሊቋቋም የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ተገንዝቦ ለመተባበር መዘጋጀት።

## VII. በዚህ መሠረታዊ ሠነድ ውስጥ የሰፈሩትን መሪ ሃሳቦች ከሚቀበሉ ግለሰቦችና የተደራጁ ኃይሎች አባላት ምን ይጠበቃል?

1. እያንዳንዱ ድርጅትና አባላቱም ከራሳቸው ጋር ታግለው የአስተሳሰብ ለውጥ ማድረግ አለባቸው፣ ድርጅቶቻቸውን ቢወዱም ከባድ መስዋዕት የከፈለለትን ራዕይ ለማዳን ከድርጅቶቻቸው ውጭ ማሰብና መሄድም ማስፈለጉን መገንዘብና ማመን አለባቸው፤

2. ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ከዚህ በፊት የጀመረውን ይቅር ተባብሎ ደመኞች የነበሩት ድርጅቶች አባላት አብሮ ለመሥራት እንደቻሉት፣ ዛሬም ቢሆን ያንን ሁሉም በየፈርጁ በተረዳው መልክ የተዋደቀለትን መሠረታዊ ዓላማ፤ አሁን በሶሽያል ዴሞክራሲ ራዕይ ማዕቀፍ የተጠቃለሉትን፤ እስከተቀበሉ ድረስ ከሁሉም ጋር ተቻችሎ አብሮ ለመሥራት መዘጋጀት አለበት። ይህ ታዲያ ትልቅ የአስተሳሰብና የሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት ያስፈልገዋል። ይህን የምናደርገው አውቀንና አምነንበትም ለዓላማችን፤ ለጋራ ራዕያችን መሳካት ስንል ነውና ጠቃሚና አስፈላጊም ከመሆኑም በላይ ታልፍ የማይቻልም ጉዳይ ነው።

3. እያንዳንዱ ይህ ጉዳይ የሚመለከተው ግለሰብ፤ ስብስብ፤ ማኅበር፤ ድርጅት ከሌሎች በርካታ ግለሰቦች፤ ስብስቦች፤ ማኅበሮች፤ ድርጅቶች አባላት ጋር አብሮ ለመሥራት ሲዘጋጅ ደግሞ ከሁሉም ታዛቢ ሊቀርብለት የሚችለውን፣ ተገቢ የሆነውን፤ በተለያዩ ወቅቶች ከራሱ ጋር በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማኅበር/ድርጅት ደረጃ ከተጋጩት ግለሰቦች ወይም ቀድሞ አብረው በአንድ ማኅበር/ድርጅት ውስጥ ኖረው በኋላ ከተለዩዋቸው/ከተጋጪቸው ጋር መልሶ የመቀራረብን ጥያቄ ሳንመልስ ልናልፈው አንችልም። ስለዚህ እነዚህ ግለሰቦች ከዋናው ጠላት ጋር እስካልወገኑና ለገራ ራዕያችን አብረውን ሊፋለሙ እስከቻሉ ድረስ አብረን ለመሥራት የሥነ ልቦና ዝግጅት ሊኖረን ይገባል።

### ማጠቃለያ

እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር በስልሳዎቹና በሰባዎቹ ውስጥ ታጋዩ ክፍል ያነሳቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች አለመመለሳቸውን የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በግልጽ

ያሳያል። እነዚህ ሕዝባዊ ጥያቄዎች መልስ እስኪያገኙ ድረስ ቀደምት ታጋዮች አሁንም በተሻለ መልክ መሰባሰብና መታገል ብሎም የሕዝብን ተስፋ ማለምለምና ሕዝባዊ ትግሉ እንዲጎለብት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በዚያን ጊዜ በትግሉ ውስጥ የተሳተፈ ኃይል ሁሉ ትግሉን በተጠናከረ መልክ ለማስቀጠል በመደራጀትና በመታገል ህያው ተግባሮች ውስጥ ሊታለፍ የማይችለውን ለለጣቂው ትውልድ የማስተላለፍ ታሪካዊ ግዴታውንም ሊወጣ ይችላልም፣ ይገባዋልም። የዚያን ትውልድ ራዕይ የማስቀጠል ትልቅ ሃላፊነትና ታሪካዊ ግዴታም አለበት ብለን እናምናለን። ስለዚህም ለማኅበራዊ ፍትህ የቆመ ኃይል ሁሉ ቀደም ብሎ የተጀመረውን ትግል ከግቡ ለማድረስ እንዲቻል ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ እሴቶቻቸውን እንደያዙ የቆዩትን ሊፈልጋቸው፣ ሊቀርባቸውና ሊጋብዛቸውም ይገባል። እናንተ ለማኅበራዊ ፍትኅ ዛሬም የምትቆሙ ሁሉ እንሰባሰብ፤ እንደራጅ፤ እንታገል ለተረካቢዎች በወጉ እናስተላልፍ እንላለን።